የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ ህዳር ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.5
ADDIS ABABA 7th December, 2023

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፰/፪ሺ፲፮
የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ....ገጽ ፲፭ሺ፪፻፷፪

**Content**

Proclamation No.1298/2023
Higher Education-, Technical and Vocational Training Research Institution and Industry Linkage Proclamation..................................................Page 15262

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፰/፪ሺ፲፮

## የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ

በሀገራችን የተጀመረውን ትምህርትና ሥልጠና ጥራትና ተገቢነት ማረጋገጥ ለምናስበው ሁለንተናዊ ብልጽግና ወሳኝ በመሆኑ፣

የትምህርትና ሥልጠና ጥራትን ለማረጋገጥ የተማሪዎችና ሠልጣኞች የተግባር ሥልጠና (ኢንተርንሽፕ)፣ የመምህራንና አሠልጣኞች የኢንዱስትሪ ተሞክሮና ጉድኝት (ኤክስተርንሽፕ)፣ የኢንዱስትሪ ሙያተኞች በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚያበረክቱት የተግባር ትምህርትና ሥልጠና አስፈላጊ በመሆኑ፣

## PROCLAMATION NO.1298/2023

## PROCLAMATION ON HIGHER EDUCATION, TECHNICAL AND VOCATIONAL TRAINING AND RESEARCH INSTITUTIONS AND INDUSTRY LINKAGE

**WHEREAS** ensuring the quality and relevance of the education and training is crucial for the holistic prosperity we envision;

**WHEREAS** the quality of education and training is ensured through internship, externship, and engagement of industry practitioners in education and training institutions skill training;

ከፍተኛ ትምህርት፣ቴክኒክና ሙያ ተቋማት እና የምርምር ተቋማት ከኢንዱስትሪ ጋር በመተሳሰር ምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግርና የማማከር አገልግሎት ሥራዎችን ማከናወን ስለሚጠበቅባቸው እና ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪ ለመገንባት ለኢንዱስትሪው ብቁ የሰው ኃይል፣ ችግር-ፈቺ ምርምር የማካሄድና ቴክኖሎጂ የማመንጨት ተልዕኮ ስላላቸው፣

የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ ምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር በጋራ ተጠቃሚነትና የትስስር አካላትን ንቁ ተሳታፊነት ስለሚጠይቅ እንዲሁም በሀገራችን ብሔራዊ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ላይ የተመላከቱ የትስስር ቁልፍ ጉዳዮችን በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፰/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/**"የማማከር አገልግሎት"** ማለት የከፍተኛ ትምህርት መምህራን፣ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት አሠልጣኞች እና የምርምር ተቋማት ተመራማሪዎች ሙያዊ ክህሎታቸውን በመጠቀም በፕሮጀክት ጥናት፣ ዲዛይንና አስተዳደር፣ በደንበኛ ምክር፣ በሥልጠና እና በእውቀት ሽግግር ላይ የሚሰጡት የፈጠራ እና የምክር ባህሪይ ያለው የሙያ ወይም የቴክኒክ

**WHEREAS** higher education-, technical and vocational training , and research institution are expected to carry out research, technology transfer and consultancy services in linkage with the industry; and their mission in generating qualified human resource, conducting applied research, transferring technology is crucial for industry competitiveness;

**WHEREAS,** higher education-, technical and vocational training-, research- institution and industry linkage requires mutual benefit and active participation of actors; and the need to legislate the linkage priority areas indicated in the national science, technology and innovation policy ;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia the "Higher Education, Technical and Vocational Training and Research Institution and Industry Linkage Proclamation is hereby issued.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Higher Education, Technical and Vocational Training Research Institution and Industry Linkage Proclamation Number 1298/2023.

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1. **Consultancy Service"** means professional, intellectual or technical advisory roles rendered by academic staff and researchers on project design, study, management, counseling, training and knowledge transfer.

አገልግሎት ነው፡፡

፪/**"የተግባር ልምምድ"** ማለት ኤክስተርንሺፕ፣ ኢንተርንሺፕ እና የትብብር ሥልጠና የሚያካትት ነው፡፡

፫/ **"ኤክስተርንሺፕ"** ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን እና የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት አሠልጣኞች በኢንዱስትሪ ውስጥ የሥራ ላይ ልምምድ እና የሥራ ቦታ ተሞክሮ እንዲያገኙ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ባለሙያዎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተግባር ልምምድ የሚሰጡበት እና ትምህርትና ሥልጠና የሚያገኙበት አሰራር ነው፡፡

፬/ **"ኢንተርንሺፕ"** ማለት የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ተማሪዎችና ሠልጣኞች በኢንዱስትሪ ውስጥ የተግባር ልምምድ እና የሥራ ቦታ ተሞክሮ ትምህርትና ሥልጠና የሚያገኙበት አሠራር ነው፡፡

፭/ **"የጋራ ተግባራዊ ምርምር"** ማለት ለምርምር በተደረገ የትብብር ስምምነት መሠረት የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክ ሙያ ሥልጠና ተቋማት ከኢንዱስትሪ፣ ከምርምር ወይም ከሌላ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ሀገር አቀፍ ወይም አካባቢያዊ ችግሮችን ለመፍታት በትስስር የሚያከናውኑት ምርምር ነው፡፡

፮/ **"የትብብር ሥልጠና"** ማለት የሠልጣኙን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ለማጎልበት በማሠልጠኛ ተቋማት የሚሰጠውን መሠረታዊ ሥልጠና በኢንዱስትሪ ከሚሰጠው ተግባር ተኮር ሥልጠና ጋር በማቀናጀት በትብብር የሚሰጡት የሥልጠና ዘዴ ነው፡፡

፯/ **"ኢንዱስትሪ"** ማለት ማንኛውም በግል፣ በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ባለቤትነት ስር የሚገኝ ሴክተር መሥሪያ ቤት ወይም በሥሩ የሚገኝ ተጠሪ ተቋም ሆኖ ለትስስር ሥራዎች በትብብርና በጉድኝት መስራት የሚችል የአምራች ዘርፍ ወይም አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ወይም ተቋም ነው፡፡

2. **"Practical Training"** means a training which includes internship, externship and cooperative training.

3. **"Externship"** means industry-based practical training offered to higher education instructors or technical and vocational training institution trainers, or provision of practical training by industry practitioners in higher education- and technical and vocational training institutions.

4. **"Internship"** means industry-based practical training offered to higher education institutions' students, or technical and vocational training institutions' trainees that help them to acquaint with the real life work place environment.

5. **"Joint Applied Research"** means collaborative research conducted among Higher Education- Technical and Vocational Training and Research Institutions, Industry, other Governmental or Non Governmental Organizations to address national or industry problem through linkages.

6. **"Cooperative Training"** means a mode of training delivered by the cooperation of higher education or technical and vocational training institutions and industry.

7. **"Industry"** means any private, public or Non-Governmental manufacturing or service providing sector with potential for partnership or linkage related works.

፰/ **"የቴክኖሎጂ ሽግግር"** ማለት በኢንዱስትሪዎች፣ በከፍተኛ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ፣ በምርምር ተቋማት እና በሌሎች በመንግስትና በግል ተቋማት መካከል የሚደረግ የሙያ፣ የእውቀት፣ የቴክኖሎጂ፣ የአመራረት ዘይቤዎችን፣ ምርት ናሙናዎችን የመለዋወጥ ሂደት ሆኖ በውጤቱም ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂካዊ እድገቶች ለተጠቃሚ የሚደርሱበትና ተጠቃሚውም ቴክኖሎጂውን ወደ አዲስ ምርት፣ ሂደት፣ ጥቅም፣ ቁሳቁስ ወይም አገልግሎት የሚቀይርበት ሂደት ነው፡፡

8. **"Technology Transfer"** means the process of sharing or utilizing skills, knowledge, technologies, methods among higher education, technical and vocational and research institutions, and other public and private organizations; and make scientific and technological outputs accessible where the end user further develops or exploits the technology into new products, processes, applications, materials or services.

፱/ **"አዕምሯዊ ንብረት"** ማለት የሰው ልጅ አእምሮ ውጤት በሆኑ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ያለ ሕጋዊ መብት ሲሆን ፓተንትን፣ የንግድ ምልክትን፣ ኮፒራይትን፣ የምዝገባ እና የግልጋሎት ሞዴል ምስክር ወረቀትን የሚጨምር ሆኖ በትስስር ሥራ ወቅት የሚገኝ መብት ነው፡፡

9. **"Intellectual Property"** means a legal right over a creative work of the human intellect and includes patent, trademark, copyright, registration, and utility model certificates obtained through linkages.

፲/ **"የምርምር ድጋፍ"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ ወይም ምርምር ተቋም ለሚካሄድ የጋራ ምርምር በኢንዱስትሪ፣ በፋውንዴሽን፣ በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት የሚደረግ የዓይነት እና የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡

10. **"Research Grant"** means financial or in-kind support provided by Public or Non Governmental Organization, for joint applied research projects conducted jointly by higher education, technical and vocational training or research- institutions.

፲፩/ **"ትስስር"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪ መካከል በዚህ አዋጅ በተደነገጉ አቅጣጫዎች፣ በጋራ ተጠቃሚነት መርሆዎች የሚካሄድ የተማሪዎችና ሠልጣኞች የተግባር ትምህርትና ሥልጠና (ኢንተርንሽፕ)፣ የመምህራንና አሠልጣኞች የኢንዱስትሪ ተሞክሮና ጉድኝት(ኤክስተርንሽፕ)፣ የኢንዱስትሪ ሙያተኞች በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚያበረክቱት የተግባር ትምህርትና ሥልጠና፣ እና በትብብር የሚካሄድ የምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግርና የማማከር ሥራዎች ጉድኝት ሥራዎች ነው፡፡

11. **"Linkage"** means a collaborative and mutual-benefit platform that help to formally establish internship, externship, joint applied research, technology transfer, consultancy service, or cooperative training activities among higher education, technical & vocational training, research institutions and industries.

፲፪/ **"የትስስር ምክር ቤት ወይም ምክር ቤት"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተመላከተውን የትስስር አካላትን ያቀፈና ትስስሩን በበላይነት የሚመራ አደረጃጀት ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፬ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የተቋቋመው ነው፡፡

፲፫/ **"የትስስሩ አካላት"** ማለት የትስስሩ ዋና ተዋንያን ሲሆኑ እነርሱም ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የኢኮኖሚ ሴክተር መሪ መሥሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የምርምር ተቋማት፣ የሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት፣ የግል አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች፣ የፌደራልና ክልል ንግድ ምክር ቤትና ዘርፍ ማህበራት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ሀገር በቀል ድርጅቶች፣ የሙያና ሲቪክ ማሕበራት እና ሌሎች በምክር ቤቱ የሚካተቱ ናቸው፡፡

፲፬/ **"ከፍተኛ ትምህርት ተቋም"** ማለት በመንግሥት ወይም በግል ባለቤትነት ሥር የሚተዳደርና በተለያዩ የትምህርት መስኮች በቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ የዲግሪ መርሐ ግብሮች የሚሰጥ፣ የጥናትና ምርምር እና የማህበረሰብ ጉድኝት ሥራዎችን የሚሠራ ተቋም ነው፡፡

፲፭/ **"የምርምር ተቋም"** ማለት በልዩ ተልዕኮ ተደራጅቶ ምርምር እና የማማከር አገልግሎት የሚያከናውን ማለት ነው፡፡

፲፮/ **"ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና"** ማለት በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በተለያዩ የሙያ ዓይነቶች ከደረጃ ሁለት እስከ ሦስተኛ ዲግሪ ባሉ ደረጃዎች ትምህርትና ሥልጠናን በመስጠት እውቀትን፣ ክህሎትንና የሙያ ሥነ-ምግባርን በማጎልበት እና በሙያ ብቃት ምዘና በማረጋገጥ ለሥራ ዝግጁ የሚደረግበት የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ማለት ነው፡፡

12. **"Linkage Council or the Council"** means an organization that consists of members referred to in Article 5 of this Proclamation and which oversees linkage activities, and established in accordance with Article 4 (1) of this Proclamation.

13. **"Linkage Stakeholders"** means main actors of the linkage which includes leading economic sectors and reporting institutions, public development enterprises, higher education, research, technical and vocational training-institutions; private manufacturing and service providing organizations, Federal and Regional Chambers of Commerce, Sectorial Associations, Non Governmental Organizations, or Professional and Civic Associations or others which shall be included by the council as required.

14. **"Higher Education Institution"** means public or private institution that offers under and post graduate study programs, and also conducts research and community engagement activities.

15. **"Research Institute"** means an organization established with special missions of conducting research and consultancy services.

16. **"Technical and Vocational Training Institutions"** means an institution that provides various Level II to third degree trainings and which prepares trainees for jobs through enhancing knowledge, skills, professional ethics and professional qualification assessment criteria.

፲፯/ **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

፲፰/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፲፱/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገጸው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

**፫. የትስስሩ ዓላማ**

የትስስር ሥራዎችን ሀገራዊ የልማት አጀንዳን ባገናዘበ መልኩ በቅንጅት፣ በወጥነት፣ በተጠያቂነት እና በብቃት በመተግበር፣ ውጤታማነትን፣ የጋራ ተጠቃሚነትን፣ ሀገራዊ እና ዓለማቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

**፬. ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ ትስስርን በሁሉም የትስስር አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ የትስስር ምክር ቤት መቋቋም፣ የምክር ቤት አባላት እና የምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

**፭. የትስስር ምክር ቤት መቋቋም**

ከከፍተኛ ትምህርት፣ ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ ከምርምር ተቋማት፣ ከኢንዱስትሪዎች እና ከመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች የተውጣጣ የትስስር ሥራዎችን በበላይነት የሚመራ የትስስር ምክር ቤት ከዚህ በኋላ "ምክር ቤቱ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**፮. የምክር ቤት አባላት**

፩/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምክር ቤቱ ሌሎች አባላትን የመጨመር ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት የምክር ቤት አባላት ይሆናሉ፣

፪/የምክር ቤቱ አባላት የሆኑት የትስስሩ አካላት የሚከተሉትን ያካትታል፣

17. **"Ministry or Minister"** means the Ministry of Education or the Minister, respectively.

18. **"Person"** means a natural or juridical person.

19. Any expression in the masculine gender includes the feminine gender.

**3. Purpose of the Linkage**

To ensure effectiveness, mutual benefit, National and International competitiveness by implementing linkage activities with coordination, consistency, accountability, and efficiency in line with the national development agenda.

**4. Scope of Application**

This Proclamation shall apply to all linkage actors.

## PART TWO
## ESTABLISHMENT OF LINKAGE COUNCIL; MEMBERS OF THE COUNCIL; DUTIES AND RESPONSIBILITIES OF THE COUNCIL

**5. Establishment of the Linkage Council**

The Linkage Council, hereinafter referred to as "the Council", is hereby established to oversee linkage activities and comprised of Higher Education-, Technical and Vocational Training and Research Institutions, Industries, Government and other Senior Officials.

**6. Members of the Linkage Council**

1/ Whereas the Council has the power to add members as deemed necessary, it shall have the following members.

2/ Members of the Council include the following:

(ሀ) ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የኢኮኖሚ ሴክተር መሪ መሥሪያ ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት፣

(ለ) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣

(ሐ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣

(መ) የምርምር ተቋማት፣

(ሠ) የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት፣

(ረ) የግል አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች፣

(ሰ) የፌደራል እና የክልል ንግድ ምክር ቤትና ዘርፍ ማህበራት፣

(ሸ) መንግሥታዊ ያልሆኑ ሀገር በቀል ድርጅቶች፣

(ቀ) የሙያና ሲቪክ ማህበራት፣

፫/ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሐፊ የሚኖረው ሆኖ ትምህርት ሚኒስቴር የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ሲሆን ከሌሎቹ የምክር ቤቱ አካላት ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡

፬/ የምክር ቤቱን አደረጃጀት እና አሠራርን የሚወስን ዝርዝር መመሪያ በሚኒስቴሩ ተዘጋጅቶ ይወጣል፡፡

**፯. <u>የምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩/ መንግሥት በሚያስቀምጣቸው የትኩረት መስኮች መሰረት የትስስር ስትራቴጂካዊ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤ የትስስሩን ዕቅድና አፈጻጸምም በበላይነት ይከታተላል፤ ይገመግማል፤

፪/ በትስስር አካላት በወል እና በተናጠል መተግበር የሚገባቸውን የትስሰር ጉዳዮች ይለያል፣ በዕቅድ ተይዘው በቅንጅት መፈጸማቸውን ይከታተላል፣ መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

a/Leading economic sectors and their reporting institutions;

b/ State Owned Enterprise ;

c/ Higher Education Institutions;

d/ Research Institutions;

e/ Technical and Vocational Training Institutions;

f/ Private Manufacturing and Service Providing Organizations;

g/ Federal and Regional Chamber of Commerce and Sectoral Associations;

h/ Non-governmental Local Organizations;

i/ Professional and Civic Associations.

3/ The Council shall have a chair, deputy chair and secretary; the Ministry of Education shall be the chair of the Council; a deputy chair and a secretary shall be from other members of the Council.

4/ A detailed Directive determining organizational structure and function of the Council shall be issued by the Ministry.

**7. <u>Powers and Duties of the Council</u>**

The Council shall have the following Powers and Duties.

1/ In accordance with priority areas of the government, set linkage strategic directions, monitor and evaluate its process and performance;

2/ Identify shared and individual linkage affairs; monitor and evaluate performances; forward directions on issues that need further improvement;

፫/ ከትስስር አካላት የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡትን ተሞክሮ ይቀምራል፣ ለሌሎች እንዲተላለፍ ያደርጋል፤

፬/ የትስስር ጉዳዮች ውጤታማ ትግበራን የሚያግዙና የሚያማክሩ አካላትን እና ግለሰቦችን እንደ አስፈላጊነቱ በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ ማሳተፍ እና እውቀትና ልምዳቸውን እንዲያጋሩ ይወስናል፤

፭/ሌሎች የትስስሩን ዓላማ ለማሳካት የሚያግዙ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የትስስሩ አካላት የወል እና የተናጠል ተግባር እና ኃላፊነት

### ፰. የትስስሩ አካላት የወል ተግባር እና ኃላፊነት

፩/ ለትስስሩ ውጤታማነት የሚሆን አደረጃጀት እና ምቹ ሁኔታ የመፍጠር፣

፪/ የትስስሩ ሥራ በየዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን የመተግበር፣ የመከታተልና ተግባራዊነቱን የማረጋገጥ፣

፫/የትስስሩ አካላት ስለሚኖራቸው ግንኙነት እና ትስስሩን ለማጠናከር የሚያስችሉ የውስጥ መመሪያ የማውጣት፣ የማሻሻል፣ ተግባራዊነቱን የመከታተል፣ የማረጋገጥ እና ምላሽ የመስጠት፤

፬/ ከትስስሩ አካላት ጋር መረጃዎችን መለዋወጥ የሚያስችል ሥርዓት የመፍጠር፣

፭/ የትስስር ዕቅድ፣ ክትትል እና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት እና በየደረጃው ላለው ለትስስሩ አስተባባሪ ሪፖርት ማቅረብ፣

፮/ የትስስር አካላትን መደበኛ ሥራ በማያስተጓጉል አግባብ መሠረተ ልማቶችን ለትስስር ሥራዎች አገልግሎት እንዲውሉ የማድረግ፤

፯/ በትስስሩ ለሚሳተፉ የተቋሙ ማህበረሰብ በትስስር ምክንያት የሚታወቅ የሌሎች ተቋማትን ሚስጥር የመጠበቅ፣ መብትና ግዴታን የሚደነግግ የውስጥ ስርዓት የመዘርጋት፤

3/ Compile and share best practices from the linkage actors;

4/ Invite stakeholders and individuals as deemed necessary to the Council meeting, and who can share their knowledge and experience, as well as assist and advice on effective implementation of linkage activities;

5/ Perform other functions that help achieve purpose of linkage.

## PART THREE
## SHARED AND INDIVIDUAL DUTIES AND RESPONSIBILITIES OF LINKAGE ACTORS

### 8. Shared Duties and Responsibilities of Linkage Actors

1/ Create an organizational structure and conducive working environment for effectiveness of the linkage;

2/ Implement, monitor and ensure effectiveness of linkage activities in their respective sector;

3/ Issue or amend guideline that facilitate and strengthen linkage among stakeholders; monitor, validate and respond to its functionality;

4/ Create a system that allow to exchange information with the linkage actors;

5/Establish linkage planning, monitoring and evaluation system; and report to linkage coordinator at at each level;

6/ Avail their infrastructure for linkage activities and in a manner that does not interfere with the regular work of actors;

7/ Establish an internal system that stipulates the rights and obligations as well as keeps confidentialities of institutions participating in linkage affairs;

፰/ በየዘርፉ ለሚፈጠሩ የትስስር ግንኙነቶች አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ እና ለምክር ቤቱ ሪፖርት የማቅረብ እና፤

፱/ ሌሎች ትስስሩን ውጤታማ ለማድረግ የሚረዱ ሥራዎችን የመፈጸም ተግባር እና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

## ፱. <u>የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩/ በተቋማዊ የስትራቴጂ ሰነዶች ውስጥ የትስስር ሥራን የማካተት፤

፪/ የትስስር ሥራን ለመስራት የሚያስችል የሰው ኃይልና በጀት የመመደብ፣ የትስስር ገቢን የማስተዳደር እና የአሠራር ሥርዓት የመዘርጋት፤

፫/ በትስስሩ ሂደት የማህበረሰቡን ችግር ትኩረት ሰጥቶ መፍታትና ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ፤

፬/ በምክር ቤቱ የተለዩ እና ቅድሚያ የተሰጣቸውን የትስስር ተግባራት መሠረት በማድረግ የተቋሙን የተልዕኮ ልየታ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም የቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ አግባብ የማቀድና የመተግበር፤

፭/ በትስስር የሚከናወን ምርምርና ፈጠራ በትስስሩ ለማሳካት የተለዩትን የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን የማረጋገጥ እና አስፈላጊውን ፈንድ በጋራ ማፈላለግ፤

፮/ በትስስሩ የሚከናወኑ ተግባራት ለትምህርትና ምርምር ጥራት፣ ለማህበረሰብ ጉድኝት፣ ለኢንዱስትሪዎች እና ኢንተርፕራይዞች ውጤታማነት በሚያግዝ አግባብ መተግበሩን ማረጋገጥ፤

8/ Provide the necessary support and monitoring; submit a report to the council; and

9/ Perform other duties and responsibilities that help make the linkage effective.

## 9. <u>Duties and Responsibilities of Higher Education Institution</u>

Higher Education Institution shall have the following duties and responsibilities:

1/ Incorporate linkage activities in its institutional strategic documents;

2/ Establish linkage operational system; allocate human power and budget for linkage activities, manage linkage incomes;

3/ Address community problems; and ensure community benefits from the linkage;

4/ Consider institution's mission and differentiation based on the Council's prioritized linkage activities; plan and execute linkage activities through participation of key stakeholders;

5/ Ensure research and innovation implementation in line with the demand of linkage actors; jointly solicit the necessary funds;

6/ Ensure linkage activities are implemented in accordance with addressing quality of education and research; as well as contributing to community engagement and effectiveness of industries and enterprises; and

፯/ በትስስር የሚገኝ የአእምሯዊ ንብረት መብት ጸንተው ሥራ ላይ ባሉ ሕጎች እና የትስስሩን አካላት መብት እና ጥቅም በሚያስጠብቅ አግባብ ለትምህርታዊ አገልግሎቶች የማዋል፡፡

**፲. <u>የምርምር ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት</u>**

የምርምር ተቋም የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት ይኖረዋል።

፩/ ትስስርን በአደረጃጀትና አሠራር ደግፎ የማከናወን፤

፪/ በትስስር የሚፈጠር ገቢን ለማስተዳደር የሚያስችል ግልጽ፣ ተጠያቂነትና ውጤታማነት የሚያረጋግጥ ሥርዓት የመዘርጋት፤

፫/ በትስስሩ የሚከናወኑ ተግባራት የኢንዱስትሪውንና የማህበረሰቡን ችግር በሚፈታ አግባብ እንዲሸጋገር ሥርዓት መዘርጋቱን የማረጋገጥ፤

፬/ በምክር ቤቱ የተለዩ እና ቅድሚያ የተሰጣቸውን የትስስር ተግባራት መሠረት በማድረግ የቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ አግባብ የማቀድና የመተግበር፤

፭/ በትስስር የሚከናወን ምርምርና ፈጠራ በትስስሩ ለማሳካት የተለዩትን የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን የማረጋገጥ፤እና

፮/ በትስስር የሚገኝ የአእምሯዊ ንብረት መብት ፀንተው ሥራ ላይ ባሉ ሕጎች እና የትስስሩን አካላት መብት እና ጥቅም በሚያስጠብቅ አግባብ ለቀጣይ ምርምር አጀንዳ በሚውል አግባብ የመጠቀም፡፡

**፲፩. <u>የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት</u>**

የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋም የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩/ ትስስርን በአደረጃጀትና አሠራር ደግፎ የማከናወን፤

፪/ በትስስር የሚፈጠር ገቢን ለማስተዳደር የሚያስችል ግልጽ፣ ተጠያቂነትና ውጤታማነት የሚያረጋግጥ ሥርዓት የመዘርጋት፤

7/ Ensure intellectual property rights obtained through linkage are used for educational services and in accordance with the laws in force and the rights and interests of the linkage actors.

**10. <u>Duties and Responsibilities of Research Institution</u>**

Research Institution shall have the following duties and responsibilities:

1/ Implement the linkage through organizational structure and practices;

2/ Establish clear, accountable, and effective system to properly manage linkage income;

3/ Ensure linkage activities are implemented through a system that address the industry and community problems;

4/ Plan and execute linkage activities based on the Council's priorities, and in a manner that ensures participation of key stakeholders;

5/ Ensure research and innovation implementation in line with the demand of linkage actors; and

6/ Ensure intellectual property rights obtained through linkage are used for further research agenda and in accordance with the laws in force and the rights and interests of the linkage actors.

**11.<u>Duties and Responsibilities of Technical and Vocational Training Institution</u>**

Technical and Vocational Training Institution shall have the following duties and responsibilities:

1/ Implement the linkage through organizational structure and practices;

2/ Establish clear, accountable, and effective system to properly manage linkage income;

፫/ ለውጤታማ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን፣ የተግባር ልምምድ፣ የማማከር ሥራ እና የትብብር ስልጠና አፈጻጸም የሚሆን ምቹ ተቋማዊ አካባቢ የመፍጠር እና የትስስሩ አካላት ያላቸውን መሠረተ ልማት ለጋራ ሥራ እንዲጠቀሙ የማድረግ፣

፬/ በትስስሩ የሚከናወኑ ተግባራት ለሥልጠናና ክህሎት ልማት፣ እንዲሁም በአካባቢው ላሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማደግና ተወዳዳሪ መሆን በሚያግዝ አግባብ መተግበሩን የማረጋገጥ፤

፭/ የትስስሩ አካላት ለጋራ ምርምር ሥራዎች አመቺ እንዲሆን ማበልጸጊያ ማዕከላትን የመፍጠር፣

፮/ በትብብር የሚከናወን የትብብር ሥልጠና፣ ፈጠራ፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር እና ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እንዲሁም የማማከር አገልግሎት፣

፯/ በትስስር የሚገኝ የአእምሯዊ ንብረት መብት ጸንተው ሥራ ላይ ባሉ ሕጎች እና የትስስሩን አካላት መብት እና ጥቅም በሚያስጠብቅ አግባብ ለሥልጠናና ክህሎት ግንባታ አገልግሎቶች የማዋል፡፡

**፲፪. <u>የኢንዱስትሪ ተግባር እና ኃላፊነት</u>**

የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡-

፩/ በተግባር ልምምድ ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎች፣ ሠልጣኞች፣ መምህራን እና አሠልጣኞች ውጤታማ ቆይታ እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ዝግጅትና ምቹ ከባቢን የመፍጠር፤

፪/ ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን፣ ለተግባር ልምምድ፣ ለማማከር ሥራ እና ተግባር ተኮር ሥራዎች የሚውል መሠረተ-ልማት የማመቻቸት፤

፫/ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን፣ የተግባር ልምምድ፣ የፈጠራ እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን ከከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና እና የምርምር ተቋማት ጋር ለመሥራት የሚያስችል የትስስር ሥርዓት የመዘርጋት፤

3/ Create conducive environment and infrastructure for effective industry extension, Practical training, consultancy service, and cooperative training;

4/ Ensure linkage training activities are implemented through enhancing skills, as well as through development and competitiveness of proximate micro and small enterprises;

5/ Establish incubation centers that facilitate joint research activities among linkage actors;

6/ Properly implement linkage's cooperative training, innovation, technology transfer, industry extension and consultancy services;

7/ Ensure intellectual property rights obtained through linkage are used for training and skill enhancement and in accordance with the laws in force and the rights and interests of the linkage actors.

**12. <u>Duties and Responsibilities of Industry</u>**

The industry sector shall have the following duties and responsibilities:

1/ Create conducive environment for students, trainees, instructors, and trainers participating in Practical training;

2/ Create conducive environment and infrastructure for industry extension, Practical training and consultancy service;

3/ Establish linkage system with higher education, technical and vocational training, and research institutions, and that help carry out industrial extension, Practical training, innovation and technology transfer;

፬/ ቅድሚያ የሚሰጠውን የጋራ ምርምር፣ ፈጠራ እና ቴክኖሎጂ ሽግግር አጀንዳዎችን መለየትና ለትስስር ባለድርሻ አካላት የማሳወቅ እና

፭/ የትስስር ሥራን ለማሳካት አደረጃጀት መፍጠር፣ በቂ የሰው ኃይል እና ሀብት የመመደብ፡፡

**፲፫. የመንግሥት የልማት ድርጅት ተግባር እና ኃላፊነት**

የመንግሥት የልማት ድርጅት የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩/ ከከፍተኛ ትምህርት፣ ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ ከምርምር ተቋማት እና ከኢንዱስትሪ ጋር ጠንካራ ግንኙነት የመፍጠርና በቅንጅት የመሥራት፤

፪/ ከዓመታዊ መደበኛ በጀታቸው ውስጥ ለትስስር ሥራዎች በጀት የመመደብ፤ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ ተዘጋጅቶ ገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፫/ በምክር ቤቱ የሚወሰኑትን የትስስር ቅድሚያ ትኩረት ጉዳዮች ልየታ ላይ የመሳተፍ እና ተግባራዊነቱን የመደገፍ፣

፬/ ከሀገሪቱ እና ከልማት ድርጅቱ የእድገት አጀንዳ ጋር የተጣጣሙ ከሌሎች የትስሰሩ አካላት ጋር በመተባበር ለምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግር ትኩረት በመስጠት ለከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ፕሮግራሞች አግባብነትና ጥራት እንዲሻሻል በማድረግ ብቁ የሰው ሀብት ልማትና ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ የበኩሉን መወጣት፡፡

4/ Identify and communicate joint research, innovation and technology transfer agenda to linkage stakeholders;

5/ Establish organizational structure, as well as allocate human power and budget to carry out linkage activities.

**13. Duties and Responsibilities of State Owned Enterprise**

State Owned Enterprise shall have the following duties and responsibilities:

1/ Build relationship and execute join linkage activities jointly with higher education, technical and vocational training, research institutions and industry;

2/ Allocate budget for linkage from annual regular budget; the detail shall be prepared by the Council and determined by a Directive issued by Ministry of Finance;

3/ Participate and support implementation of linkage priorities decided by the Council;

4/ Ensure the development of qualified human resource and industry competitiveness in line with the national development agenda; together with other linkage actors give due attention to research, and technology transfer qualities and relevance at higher education-, technical and vocational training- institutions .

**፲፬. <u>የትምህርት ሚኒስቴር ተግባር እና ኃላፊነት</u>**

የትምህርት ሚኒስቴር ሀገራዊ የትስስር ሥራዎች አስተባባሪ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩/ በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙ.ያ ሥልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ በጋራ የሚያካሂዱ የትስስር ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ የትስስር ምክር ቤቱን በሰብሳቢነት ይመራል፣

፪/ ከትስስር አካላት ጋር በመሆን የትስስር ጉዳዮች ቅድሚያ ትኩረት አጀንዳ እና የትስስር ፍላጎትን በመለየት የትግበራ ስልት ይቀይሳል፤

፫/ የትስስር አካላት በምክር ቤቱ የተቀመጡ አቅጣጫዎችን በእቅድ አካተው መተግበራቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡ የተሻለ አፈጻጸም ያሳዩትን ተሞክሮ ለሌሎች ያጋራል፣ የእውቅናና ማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፤

፬/ የትስስር ጉዳዮች አተገባበር የሚደነግግ ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት ለትስስር ምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ያጸድቃል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

፭/ ትስስሩን ሊያጠናክር የሚችል፣ ሀብት የሚመነጭበትና በትስሰር አካላት ለሚከናወኑ ተግባራት የሚውልበት የትስስር ፈንድ አሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከምክር ቤቱ ጋር በመሆን ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል።

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>አዕምሯዊ ንብረት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር</u>

**፲፭. <u>የአዕምሯዊ ንብረት አፈጻጸም</u>**

የትስስር አካላት በትስስር የሚገኙ የአዕምሯዊ ንብረት ውጤቶች ባለቤትነት መብት እና አስተዳደር ሥርዓት በተመለከተ ጸንተው ባሉ ሕጎች መነሻ ትስስርን ታሳቢ ባደረገ አግባብ ዝርዝር መመሪያ ያዘጋጃሉ፡፡

**14. <u>Duties and Responsibilities of Ministry of Education</u>**

The Ministry of Education, which is national coordinator of the linkage, shall have the following duties and responsibilities:

1/ Nationally coordinate, support, and monitor linkage activities among higher education, technical and vocational training, research institutions and industry ; chair of the national linkage Council;

2/ In collaboration with other actors, identify linkage demands and design implementation strategic directions;

3/ As per the directions set by the Council, monitor and support linkage actors' plan and implementation activity; share best experiences to others actors; establish recognition and encouragement system;

4/ Prepare linkage affairs implementation draft Directive.; submit the same to the Council; monitor its approval and subsequent implementation; and

5/ Establish linkage fund system; mobilize resources that can strengthen linkage activities among actors; follow its proper implementation with the Council.

## <u>PART FOUR</u>
## <u>INTELLECTUAL PROPERTY AND TECHNOLOGY TRANSFER</u>

**15. <u>Intellectual Property</u>**

In accordance with the Powers and Duties detailed Directive entrusted with existing laws, linkage actors shall prepare ownership and management system of intellectual property obtained through linkage.

**፲፮. የአዕምሮአዊ ንብረት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ድጋፍ ማዕከል ስለማቋቋም**

የትስስር አካላት በትስስር የሚገኙ የአዕምሯዊ ንብረት ውጤቶች ባለቤትነት መብት እና አስተዳደር ሥርዓት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር በተመለከተ ጸንተው ባሉ ሕጎች መነሻ ትስስርን ታሳቢ ባደረገ አግባብ ዝርዝር ሥርዓት ይዘረጋሉ፡፡

**፲፯. የገቢ ክፍፍል**

በትስስር የሚገኝ የአዕምሯዊ ንብረት ገቢን በሚመለከት በትስስር አካላት እና ፈጠራ ባለቤቶች መካከል ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን ባገናዘበ መልኩ ዝርዝር መመሪያ በትስስር ምክር ቤቱ ይወጣል፡፡

**ክፍል አምስት**

**የእውቅና እና የማበረታቻ ሥርዓት**

**፲፰.ለግል ኢንዱስትሪ የሚደረግ የእውቅና እና የማበረታቻ ሥርዓት**

በትስስር የሚሳተፍ የግል ኢንዱስትሪ የሚከተሉትን እውቅና እና ማበረታቻ ያገኛል፡-

፩/ የግል ኢንዱስትሪ ከትስስሩ የሚያገኛቸው ጥቅሞች እንደተጠበቁ ሆነው ልዩ የእውቅና ሽልማት እና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው ትስስሩን የሚያጎለብት ማበረታቻ ሊያገኝ ይችላል፤

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተጠቀሰው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ለትስስሩ መሳካት ድጋፍ የሚያደርግ፣ በጋራ ሥራው ላይ ተሳታፊ የሆነ ወይም ሳይሆን ወጪዎቹን በሙሉ ሆነ በከፊል የሚሸፍን የግል ኢንዱስትሪ የሚያገኘውን ማበረታቻ በተመለከተ ሚኒስቴሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር እያቀረበ ያስወስናል፤

፫/ በግል ኢንዱስትሪ የተግባር ልምምድ ወቅት በተማሪዎች፣ በሠልጣኞች ወይም በኢንዱስትሪ ንብረት ላይ ለሚከሰት ጉዳት ማካካሻ የኢንሹራንስ ሽፋን የሚገባ ሆኖ ወጪው ከትስስር ፈንድ የሚሸፈን ይሆናል፤ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በሚያዘጋጀው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**16. Establishing Intellectual Property and Technology Transfer Support Center**

Linkage actors shall establish a system of ownership rights and management of related intellectual property products based on established laws in force regarding technology transfer based on an appropriate and detailed system.

**17. Royality Distribution**

The council shall issue a detailed Directive on fair distribution of intellectual property income between linkage actors and intellectual property owners.

**PART FIVE**

**RECOGNITION AND INCENTIVE SYSTEM**

**18.Recognition and Incentive System for Private Industries**

Private industry participating in linkage shall receive the following recognition and incentives:

1/ Subject to benefits from linkage, a private industry may receive a special recognition award and other appropriate incentives that enhance its engagement in linkage;

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Minister shall submit to the Ministry of Finance an incentive mechanism to private industry that partially or fully covers linkage costs;

3/ Compensation for damage to students, trainees, or industry property during internship shall be subject to insurance coverage and the cost shall be borne from the linkage fund; the details shall be determined by the Directive prepared by the Ministry with the relevant bodies.

**፲፱. ለግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚደረግ እውቅና እና ማበረታቻ**

በትስስር የሚሳተፍ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚከተሉትን እውቅና እና ማበረታቻ ያገኛል፡-

፩/ በትስስሩ ለሚሳተፍ የግል ኢንዱስትሪ የሚደረገው ማበረታቻ እንደሁኔታው ለግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋምም ተፈጻሚ ይሆናል፤

፪/ ከላይ በንዑስ-አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመምህራን እና የአመራሩ አቅም መገንባት እና በመንግሥት በተመረጡ የምርምር የትኩረት መስኮች የጋራ ምርምር እንዲሰሩ አስፈላጊው ድጋፍ ሊደረግለት ይችላል፡፡

**፳.በትስስር ተሳታፊ ለሆነ ተመራማሪ ወይም የፈጠራ ባለቤት የሚደረግ እውቅና እና ማበረታቻ**

በትስስር የሚሳተፍ ተመራማሪ ወይም የፈጠራ ባለቤት እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን ማበረታቻ ያገኛል:-

፩/ በትስስሩ ውስጥ በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ ምርምር ተቋም ለሚደረግ የምርምርና ፈጠራ ሥራ ተመራማሪ ከተቋሙ በጀት ውጪ ማለትም ከአገር ውስጥ ወይም ከአገር ውጭ የገንዘብ ድጋፍ የሚያስገኝ ከሆነ ከተገኘው ገንዘብ ተጠቃሚ ይሆናል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ-አንቀጽ (፩) ላይ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በፕሮጀክት ስምምነት ላይ በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል።

፫/ በሌሎች ጸንተው ባሉ ሕጎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ሴቶች እና ተጋላጭ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚደረግ ልዩ ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ በትስስር ለሚሳተፉ አካል ጉዳተኞች፣ ሴቶች እና ተጋላጭ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ተጨማሪ ድጋፍና ማበረታቻ የሚደረግ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

**19. Recognition and Incentive System for Private Higher Education Institution**

A private higher education institution participating in linkage shall receive the following recognition and incentives:

1/ The incentive mechanism stated for private industry may also apply to a private higher education institution, depending on the circumstances;

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) above private higher education institution are entitled to get capacity building to managers and instructors; and support to conduct join applied research on nationally prioritized themes.

**20. Recognition and Incentive System for a Researcher or Inventor Who Participates in Linkage**

Researcher or inventor participating in linkage activities shall receive the following incentives as appropriate:

1/ A researcher or inventor working in higher education, technical and vocational training, or research institute and securing fund from external sources and mobilizing it to the host institution shall financially be benefited from the fund; the details shall be determined by Directive.

2/ The amount of money mentioned in Sub-Article (1) shall clearly be stated in the project agreement.

3/ Without prejudice to other applicable laws, additional support and encouragement shall be provided to persons with disabilities, women and vulnerable groups participating in linkage; the details shall be determined by the Directive.

፬/ በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱ ማረበታቻዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በኤክስተርንሺፕ ለሚሳተፉ ሙያተኞች በትስስር ያላቸው አፈጻጸም ለደረጃ እድገትና ተጨማሪ ማበረታቻዎች እንዲውል ሊደረግ ይችላል፣ ዝርዝሩ የትስስር አካላቱ በሠራተኛ አስተዳደር ሕጎቻቸው ይወስናሉ፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፩. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው የትስስር ዓላማን ለማሳካትና ለአዋጁ ተፈጻሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፪. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አዋጁን ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣ ደንብን ለማስፈጸም ከምክር ቤቱ ጋር በመተባበር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፫. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, linkage activity performances shall be incorporated in career promotions and incentives; the details shall be determined by administrative employee laws of linkage actors.

## PART SIX

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**21. Obligation to Cooperate**

Every person shall be obliged to cooperate in linkage objectives and implement this Proclamation.

**22. Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue Regulation enforce the Proclamation.

2/ The Minister may issue Directive in cooperation with the Council for the implementation of this Proclamation and Regulation issued pursuant to this Proclamation.

**23. Non Applicable Laws**

Any Proclamation, Regulation, Directive or Customary practice that is inconsistent with this Proclamation shall not apply to matters covered by this Proclamation.

**24. Effective Date**

This Proclamation shall come in to force from the date of its publication on the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 7th Day of December, 2023**

**SAHLE - WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**